# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 2 ቁጥር 3 ነሐሴ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ.ም.

## የኢሕአፓ 40ኛ ዓመት ምሥረታ

*(ኢሕአፓ የታወጀበትን 40ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*



. . . አርባ ትልቅ ዓመታት

ኢ.ሕአፓ! ኢ.ሕአፓ!
የዕድሜ ደቂቅ
የገቢር የትግል ሊቅ፣
ታጋይ ልጆችህ ደምተው
ቀይ ልጆችህ ቆስለው
ላብ አደሮችህ በእሳት ነፍረው
አርሶ አደሮችህ በማጥን ነኩረው
ከፋሽስቶች የስራይ ዓይን
ከኬጂቢ የስራይ ዓይን
ከምዕታት፣ ከርግማናቸው
ከባዙቃ ከመድፋቸው
ከታንክ መትረየሳቸው
ከሚግ፣ ከሚራዣቸው
ሊሾሽጉህ፣ ሊደብቁህ
በመሃልት ሰልፍ ወጥተውልህ
ማህሌት ዘብ ቆመውልህ
በአጥንታቸው በሥጋቸው
ሥጋና አጥንት ያለበሱህ. . .ኢ.ሕአፓ!

ኢ.ሕአፓ!
እናቶች ልጃችን ያሉህ
አባቶች አንድዬ ያሉህ
እህቶች ወንድሜ ያሉህ
ታናሾች ታላቄ ያሉህ
ወንድም ጋሼ፣ ወንድም ዓለም
ኢያ ኩራቴ ያሉህ፣
ወንድም ጥላዬ ያሉህ
ድኩማን ምርኩዜ ያሉህ
ምህመናን በፈንታቸው
እስላም ክርስቲያኖች
እደግ! ተመንደግ! ያሉህ
እንትፍትፍ ብለው የመረቁህ
ፈርጥም! ለምልም! ያሉህ . . . ኢ.ሕአፓ!

ኢ.ሕአፓ! ይኸው ዛሬ አርባ ዓመትህ
ይኸው ዛሬ አርባ ዓመትህ
አርባ ትልቅ ዓመታት

ጓዶቻችን በከተማ
በፋሽስቶች የፋስ ዓመጽ
እንደ ስጋ ተኮልኩለው
እንደ ጎመን ተቀርድደው
እንደ ሽንሽን ተሸንሽነው
እንደ ክትፎ ተከትፈው
በከላሾች የጣር በትር
ዓይኖቻቸው ተደንቁለው
ጥፍሮቻቸው ተመንግለው
ምሥማር በግምባራቸው፤ እንደዋዛ ተቸንክሮ
ስንጥር በጉሮሮዋቸው፤ እንደዘበት ተሰንጥሮ
ሴቶቻችን በከተማ በኮረንቲ ጡቶቻቸው ሲነዘሩ
በጋለ ብረት ህጋቸውን ሲደፈሩ
ወፌ ላላ ተዘቅዝቀው ሲጠበሱ
በመርዝ ጢስ በአዲስ ጎጆ ሲታፈኑ
ተሰውፈው በአፋኝ ባንዳ ሲረሸኑ
የሰውን ክብር እንዳይከብሩ ሲገደሉ
የሰውን ሞት እንዳይሞቱ ሲታረዱ
ደማቸውን በልህ አፍነው
“ተኩን!” ብለው ታጋዮችን እየጠሩ
“ኢ.ሕአፓ ያቸንፋል!”
“ምዝብሩ ሕዝብ ያቸንፋል!”
እያሉህ በሙታቸው የተኩህ
በደማቸው ያፀደቁህ . . . ኢ.ሕአፓ!

ኢ.ሕአፓ!
የጉጂ የወላይታ፣ የቢቸና አርሶ አደሮች
የሐረር ቆቱ ቡላዎች፣
የአርሲ እርቦ ሰፋሪዎች
የሃዲያ የከምባታ የአሬሮ እምቢተኞች
የጎጊ የጃንጀሮ የከፋ ቀይ ቃፊሮች
የአሳይታ ከብት አርቢዎች
የአፋር ደፋርተኞች
የሰሜን የበለሳ የጠለምት ዓመጽ ለባሾች
አንተን ብለው፣ አንተን አምነው
ደጀንህን ተሸክመው
ሰንደቅህን ያቀለሙልህ
ሕይወትህን ያኖሩልህ . . . ኢ.ሕአፓ!

ኢ.ሕአፓ!
ያቃቂ የበሰቃ፣ ያዲስአባ ላብ አደሮች
የድሬ ሸመንተሪያ፣ የኮተኒ ጉፍሃኖች
የወንጂ የተንዳሆ የአዋሽ በረከተኞች
የወሊሶ የወልቂጤ፣ የአስበ ተፈሪ ጀግኖች
የመስከረም 68 ወጣት መስከረምተኞች
የደሴ፣ የአርባምንጭ፣ የጐንደር አፍላ ወጣቶች
አንተን አቅፈው፣ ትግል ሸተው
አንተን ይዘው ትግል ታግለው
ወርቃማውን መዶሻህን
ቀይ ዓርማህን ተሸክመው
ሰንደቅህን ያቀኑልህ
በደማቸው፣ በአጥንታቸው ትንፋሽ የሰረጹብህ
አውቀው እያሳወቁህ፣
ወደው እያስወደዱህ፣
አቅፈው እያሳቀፉህ፣
ባጥንታቸው፣ በሥጋቸው
ሥጋና አጥንት ያለበሱህ. . .ኢ.ሕአፓ!

ኢ.ሕአፓ!
ይኸው ዛሬ አርባ ዓመትህ

በኋላ ቀሩ ፊውዳላዊ ሥርዓት ላይ ያነጣጠረው የየካቲት 1966 ዓ.ም. ግብታዊ እንቅስቃሴ ውልደቱን ያፋጠነለት መሪ ድርጅት ኢሕአፓ የታወጀበት 40ኛ ዓመት። አርሶ አደሩ በባላባታዊ ሥርዓት ከሚደርስበት ግፍና መከራ ለመላቀቅ፣ ላብ አደሩ ቅጥ ካጣ ብዝበዛና ጭቆና ለመላቀቅ፣ ሠራተኛው ክፍል ለተመጣጣኝ የደሞዝ ክፍያና ለሥራ ዋስትና፣ መምህራን፣ ወታደሩ፣ ታክሲ ነጂው ያጀቡት ሕዝባዊ ዓመጽ የወለደው ፓርቲ ኢሕአፓ 40ኛ ዓመት። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና መብት መረጋገጥ ከዱላና ጥይት ጋር እየተጋፈጠ ለዓመታት የታገለው ተሜ የዴሞክራሲ መብትና የሕዝብ መንግሥት ጥያቄው መፍትሄ የሚያገኘው በተቀናጀ መልኩና በተደራጀ ኃይል መሆኑን በመረዳት ለምስረታው አስተዋጽዎ ያደረገበት ፓርቲ ኢሕአፓ የታወጀበት 40ኛ ዓመት።

በወቅቱ በነበሩ ተራማጅና ሀገር ወዳድ ኃይሎች ቅድመ ምሥረታውን በ1964 ዓ.ም. በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት (ኢሕአድ) በመባል ጥንስስ ምሥረታው የተተከለበት ችግኝ አብቦ እራሱን ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ልክ የዛሬ አርባ ዓመት ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. ነበር። አርባ በጋ፣ አርባ ክረምት ቆጥረን ታሪኩን እንዘክራለን። ለትውልድ እናስተላልፋለን።

ሆ! ኢሕአፓ ትውልድ ሁሉ በበጎ ያነሱሃል። ባይሳካልህም የትግል ሀሁ አስተምረሃል። ኢሕአፓ ሆይ! ታሪክህ ከነ ስህተቱ አስተማሪ ነው። ኢሕአፓ ሆይ! ታስተክዛለህ፣ ብዙሀን ሲያስቡህ ዓይናቸው ዕምባ ይሞላል። የበርካታ እምቡጥ አበባዎች ደምና አጥንት ተሸክመሃል። የበርካታ ቤተሰቦች መኖሪያ ሆነሃል። ያንተን ዕንባ እናቶች እረጭተዋል። ባንተ ትካዜ አባቶች አቀርቅረዋል። ወላጆቻቸውን የተነጠቁ የትላንት ሕፃናት ይፈልጉሃል። ታሪክህ ይኖር ዘንድ ወጣቶች "ኢሕአፓ ወይም ሞት!" ብለው አሸልበዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲ መብት ያለገደብ በትግላቸው ይቀዳጁ ዘንድ አጥርና ግድግዳዎች "ኢሕአፓ ያቸንፋል!" አድምቀው አታግለዋል። የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ስምህ ሲጠራ ይወዛወዛሉ። የሕዝብ መንግሥት ይቋቋም ዘንድ በኢሕአፓ መሪነት የጮኹ ሁሉ በዓይነ ህሊናቸው ወቅቱን ያስቡታል። የ40 ዓመት ትዝታ።

እስላም ከክርስቲያኑ፣ በዘር ሳይሆን በክፍለ ሀገር የተዋቀርከው ትስስሩ ኤርትራና ትግራይ፣ ወለጋ፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ሐረር ድሬዳዋ፣ ሲዳሞና አሩሲ፣ ጋሙ ጎምጎፋ፣ ኢሉባቡር፣ ከፋ፣ ባሌ፣ ሸዋ በአንድ ሀገራዊ ዓላማ ያሰለፈና ያታገለ ቀዳሚ ፓርቲ ኢሕአፓ!

ኢትዮጵያ ሀገራችን የሁሉም ዜጐቿ ትሆን ዘንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችን ማስወገድ አስፈላጊ ነበርና ነው ሕዝብ ዓፄው አገዛዝ ላይ ያመፀው። የደርግ አገዛዝ በሀገሪቷና ልጆቿ ላይ ያወረደው ግፍና መከራ የንጉሳዊ አገዛዝን በጐ ጐን ቢያጎላውም ከመብት አንጻር፣ ከነበረው አስከፊ የመሬት ስሪት አንፃር፣ ከወሎ ረሃብ አኳያ የዓፄ ኃ/ሥላሴ ሥርዓት ማብቃት ተማሪ ያመጣው ጣጣ ሳይሆን ረሃብ፣ ድንቁርና፣ በሽታ፣ ብዝበዛ፣ ድህነት ጐረቤቱ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘመናት መከራና ግፍ የወለደው ክስተት ነው። ዛሬ ሀገራችን በዘር ፖለቲካ ተወጣጥራ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጠሏ አጠያያቂ በሆነበት ደረጃ ሀገርና ሕዝብ

ፈጅቶ ለዘረኞች ሸጧት የፈረጠጠው ፋሽስት ደርግና መንግስቱ ኃ/ማርያም ይሻል ነበርን መስማቱን ሀገር ቢዘገንናትም እየታዘብን ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» የያ ትውልድን ታሪክ ለትውልድ ማስተላለፍ አንዱ ተልዕኮው ነውና ኢሕአፓ ለታወጀበት 40 ኛ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ እንላለን። ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ ቋንቋ ኢትዮጵያና ልጆቿ የኢሕአፓን ፕሮግራምና ዓላማ አነበቡ። ለዓለም በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋ ተሰራጨ።

እምቡጥ አበባ ኢሕአፓ! ትውልዴ ከሕዝብ አለ። የዘር ግንዴ ከጭቁኑ አለ። ቋንቋዬ ኢትዮጵያ አለ። ከበላዩ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማው ተውለበለበ። ማጭድና መዶሻ ዓርማው ከፍ አለ። ኢሕአፓ በሕዝብ ታጅቦ ለሕዝብ መብት ሊሟገት፣ የሀገርን አንድነት ሊጠብቅ ቃል የገባበት 40 ዓመት ትዝታ።

ኢሕአፓ በመስከረም ወር አደይ አበባ ደመቀ። የኢሕአፓ ብስራት በመስቀል ወፍ ዝማሬ ታጀበ። የመስከረም ፀሐይ ኢሕአፓን አደመቀች። ኢሕአፓ የሆያ ሆዬ ችቦ ለኮሰ። ኢሕአፓ ለ1968 ዓ.ም. አዲስ መት

ሆ! ብዬ መጣሁ ሆ! ብዬ
ነፃነትን ብዬ
ኢትዮጵያን ብዬ፤
አበባየሽ ሆይ . . . . . . ለምለም
የኢትዮጵያ ልጆች . . . ለምለም
ቁሙ በተራ . . . . . . ለምለም
ዝናር ታጥቁ . . . . . . ለምለም
ትግል ልመራ. . . . . . ለምለም
ትግል መርቼ . . . . . .ለምለም
ለድል በቅቼ. . . . . . . ለምለም
ሀገር ላኮራ . . . . . . . ለምለም
ሕዝብ እንዲመራ. . . . ለምለም
መብትን ልዘራ . . . . . ለምለም
ሀገር ቦርቃ . . . . . . . . ለምለም
እስከወዲያኛው . . . . . ለምለም
ሊያከትም ሰቆቃ . . . . . ለምለም
አበባ የኢሕአፓ ሲሳይ
ኮለል በይ።
አበባ ኢሕአፓ ያላችሁ
እንያችሁ። ብሎ በየቤቱ ዘመረ። እራሱን ይፋ አደረገ።

ኢሕአፓ እራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ይፋ ባደረገ ዓመት ውስጥ ተዓምር ሊፈጥር የሚችል ኃይል አሰባሰበ፣ አደራጀ። የወቅቱ ተራማጅ ኃይሎች በአብዛኛው ኢሕአፓን ከበቡ። ጊዜያቸውንና ሕይወታቸውን በኢሕአፓ ጥላ ሥር ለእምዬ ኢትዮጵያና ለሚወዱት ሕዝባቸው ሰጡ። "ፍፁም ነው እምነቴ፣ ለትግሉ ነው ሕይወቴ" ብሔራዊ መዝሙራቸው

ቋንቋቸው ሆነ። አዛውንት እናቶች አባቶች ጨምሮ ወጣቶች፣ ታዳጊ ሕጻናት፣ ወጣት ሴቶች፣ እስላም ክርስቲያኑ በኢሕአፓ ዙሪያ ለትግል ተሰለፉ። ሁሉም "የሕዝብ መንግስት" ጥያቄውን ከፍ አደረጉ፣ የ"ዴሞክራሲ መብት ያለገደብ" መፈክር አየሩን ሞላው። "የብሔር/ብሔረሰቦች መብት፣ የሴቶች እኩልነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ ለተመጣጣኝ ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ" ጥያቄዎች በወጣቶችና ተማሪዎች ታጅበው አደባባይ ብቅ አሉ። በምርጥ መኮንኖች አቅጣጫውን የሳተው የ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይመለስ ዘንድ ትግሉ በኢሕአፓ መሪነት ቀጠለ።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ ጥያቄ የዓፄው አገዛዝ የፈጠረውን ረሃብ፣ ድህነት፣ ድንቁርና እና አፈና ለመላቀቅ እንጂ ወደ ሌላ አፋኝና ገዳይ አገዛዝ ለመሸጋገር አልነበረምና እያቆጠቆጠ ያለው ፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ ላይ ሁሉም ጩኸቱን አሰማ፣ ተቃውሞው ቀጠለ። የሥርዓት ለውጥ ጠያቂው ትውልድ ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ለተውጣጣ የሕዝብ መንግሥት ምሥረታ የተጠናከረው ትግልና የመፈክሩ ወቅታዊነት ኢሕአፓን አደመቀው።

"ኢሕአፓ ነው እኮ ኢሕአፓ<br>የላብ አደር መሪ<br>ሀቀኛ ተጠሪ" አሰኘለት።

ትግሉ እየፋመ እየከረረ መጣ። ኢሕአፓና ሕዝብ በአንድ በኩል ፋሽስትና ባንዳ ምሁራን በሌላ በኩል ተፋጠጡ። 1968 ዓ.ም. የትግሉ አውራ በመሆን ወደ 1969 ዓ.ም. የተሸጋገረው ትግል የኢሕአፓን የአመራር ብቃት ጠያቂ ሆነ። በተለይ ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. የፋሽስት መንግስቱ ኃ/ማርያም መፈንቅለ ደርግ ለኢሕአፓ ደወል ነበር። ፓርቲውን ለማጥፋት መስከረም 6 ቀን 1969 ዓ.ም. የወጣው የጦርነት አዋጅ ቅድመ ዝግጅት በደርጉ ውስጥ የነበሩትን ቅን አሳቢዎች መደምሰስ ነበርና ብርጋዴል ጀነራል ተፈሪ ባንቴን ጨምሮ የተገደሉት ሰባት የደርግ አባላት ሀገሪቷን "በሞግዚት አስተዳደርነት" ከተረከቡት 120 የደርግ አመራርነት ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን፣ ፋሽስት፣ ገዳይ መንግስቱ ኃ/ማርያም እጅ ጣላት።

ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. ደም የተሞላበት ጠርሙስ ከመሬት ያገናኘው ግራዚያኒ መንግስቱ የደም ጥማቱ ማርኪያ አሰሳ፣ ነፃ እርምጃ፣ ቀይ ሽብር ሂደቶች በዘመቻ መንጥር፣ በዘመቻ ደምስስ፣ አፋኝና ገዳይ ቡድኖች ተቀነባበረ። ኢሕአፓን ለማጥፋት ሕዝብና ልጆቹ ላይ የፋሽስቶች ጥይት ዘነበ። ኢሕአፓ ከሚያስመዘግበው ድል ይልቅ የሚያጣቸው አመራር አካላቱና አባላቱ ቁጥር ሊታመን በማይችል ሁኔታ እውን ሆነ። ትግሉ ታሪክ ሆኖ ቀረ። ቋንቋ ሊገልፀው ከሚችለው በላይ ተመታ፣ ተኮላሸ።

የኢሕአፓ "ፋሽስትን ማን ይፈራዋል፣ ትግል ምኑን ትግል ሆነ፣ ማን ደባለቀው፣ ወዘተ" ግጥሞች ታሪክ ሆነው ቀሩ። "በትግል መሞት ሕይወት..." ዝማሬ እየዘመሩ ያሸለቡ ሰማህታት ይዘውት ሄዱ። "ኢሕአፓ ወይም ሞት" እያሉ ያሸለቡ ወጣቶች ደም ፀፀትን ጥሎ አለፈ። "የትግሉ ነው ሕይወቴ..." ስደትን ወለደ። "የታጋይ እረፍቱ ሞቱ..." ፍርሃትን

አበቀለ። "አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ!..." ዝማሬ እግር ብረቶችን ወለደ። ዓይኖች ሬሳ ተመልካች ሆኑ፣ ጆሮዎች ሰቆቃን አድማጭ ሆኑ፣ አፎች ተለጐሙ። ከዛሬ ነገ የሕዝብን ድል አበሰረ የተባለለት ፓርቲ ታሪክ ሆኖ ቀረ።

ባይሳካለትም ለሀገሩና ለሕዝቡ መስዋዕትነትን የከፈለ ትውልድ ታሪክ ለኢሕአፓ ሀብቱ ነው። ኢሕአፓን ለማጥፋት ደርግ ትውልድ ጨረሰ። እንደ "ፍፁም ነው እምነቴ" መጽሐፍ አገላለጽ

"ደርግ አንድ ብርቅዬ ትውልድ ጨረሰ። ሀገሪቷ በድህነት አቅሟ ለልማትና ለዕድገት የኰተኰተቻቸውን ልጆቿን ደርግ በላ። ለሕዝብ መብትና ነፃነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ልጆቿን እምቡጥ አበባዎቿን ኢትዮጵያ ተነጠቀች። መመኪያ ልጇን አጣች። ኢትዮጵያዊነት ኩራቷን፣ መለያ ክብሯን ጥቁር ድባብ አጠላባት። እምቢኝ ለመብቴ፣ እምቢኝ ለሀገሬ፣ እምቢኝ ለሕዝቤ ያለ ትውልድ በጥይት ተለቀመ። እየታነቁ ተገደሉ። በቁማቸው ከገደል አፋፍ ተወረወሩ። ወደ ባህር ተጣሉ። ሕጻናት ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እያዩ እንዲያድጉ ተገደዱ።"

የኢሕአፓ ታሪክ የሕዝብና የሀገር ታሪክ ነውና ዛሬ ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 40ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ «ያ ትውልድ ተቋም» ሰማዕታት ወገኖቻችንን እያስታወስን እናከብረዋለን። የትግላችን ጠንካራም ደካማም ጐኑ ለትውልድ አስተማሪ ነውና ከታሪክ መዝገብ ይሰፍር ዘንድ የምናደርገው ጥረት ይቀጥላል። ለትውልድ ሁሉ የያ ትውልድን ለሀገሩና ለሕዝቡ ያደረገውን ትግልና የተከፈለውን መስዋዕትነት ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውና እውነተኛው ታሪክ ሳይዛባና ሳይጋነን ይተላለፍ ዘንድ ታሪኩን የሚጽፉትን በርቱ እያልን በመፃፍም ሆነ በተለያየ መልክ ለምትጥሩ ሁሉ «ያ ትውልድ ተቋም» የአቅማችንን እገዛና ትብብር እንደምናደርግ ልናሳውቅ እንወዳለን።

ከነበረው ኋላ ቀር ሥርዓትና መረጃ እጦት የሀገራችንን፣ የሕዝባችንን ብሎም የዓለምን ነባራዊ ሁኔታና ቀደምት ታሪክ በሚገባ ካለመረዳትና ካለማወቅ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ላለመድገም የነበርንበትን፣ የምናውቀውን የራሳችንን ታሪክ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ እንጣር። የያ ትውልድ የትግል ታሪክ አስተማሪነቱ አጠያያቂ አይደለምና ቀደምት ታሪክን አውቀውና ተዘጋጅተው ለወደፊቱ አቅጣጫ ሊሰጥ የሚችል መሪ ዜጋ ሀገርና ሕዝብ ያወጡ ዘንድ ጥረታችን ይቀጥላል።

«ያ ትውልድ ተቋም» የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የታወጀበትን አርባኛ ዓመት ስናስታውስ በትግሉ የተሰዉ ወገኖቻችንን እየዘከርን ነው። የታሪኩ ተጋሪ በመሆናችን እንኮራለን። ባይሳካልንም ለትግሉና ለኢሕአፓ ያፈሰስነው ደም፣ የከሰከስነው አጥንት ኢትዮጵያን ይጠብቃታል።

ኢሕአፓ በአጥንትና ደም የተገነባ የሀገርና ህዝብ ሀብት ነው!!!

«ያ ትውልድ ተቋም»

ኢሕአፓ !

ከባሩድ ባሩድ ሰልቆ
ከቃታ ቃታ ፈልቅቆ
ከርችት እርችት ተኩሶ
ከትንታግ ትንታግ በጥሶ
የዋእይታ፣ የእሪታ፣ የዕምባው ዱር
የየዬ፣ የሎሄ፣ የወዮ ዓለም የግፍ ጌጡ
የሰቀቃ እምቡሽቡሹን
የኮሶ እሬት ድፍድፉን
አክ! እንትፍ! ለአንዴም ለሁሌም
ዬጭ! በቃኝ! ዓለም ዘላለም
ትግል ሕይወቴ ሞቴ
ትግል ሞቴ ሕይወቴ
ትግል ብሎ ኢሕአፓ
የላብ አደር ፓርቲ
አደባባይ የወጣበት
ለወዳጅም ለጠላትም
ለዘመድም ለባዕድም
ለትልቁም ለትንሹም
ሆ! ለጭቁን የጮኸበት
ቼ! ለምዝብሩ ያዜመበት
የምሥራች ያገኘበት
እነሆ ዛሬ አርባ ዓመት
. . .እነሆ ዛሬ አርባ ዓመት።

ኢሕአፓ!
ሀገር ቀይ በቀይ ደምቆ
ከአድማስ አድማስ አሽብርቆ
ሣር ቅጠሉ ተሽቆጥቁጦ
ምድር ሰማዩ አጊጦ
በኢሕአፓ የዓመጽ ግርማ
የግፉሃን የደም አርማ
ያገር ወንድም፣
ያገር እህት፣
ያገር እናት፣
ያገር አባት
ያገር አጎት
ያገ አክስት
በቀይ አደይ ተከሽኖ
በዓመጽ መዝሙር ተጀንኖ
ባሻፈረኝ ቀረርቶአቸው
በጦርም አንደበታቸው

ኢትዮጵያችን ውበት ለብሳ
መንደራችን እሳት ልሳ
ተወጥራ፣ ተሰልቃ
እንደ እንዝርት ሽራ፣ ተሰብቃ
ያረገደች የዘፈነች የተገዘፈችበት
እየተውረገረገች፣እየተምዘገዘገች
እየተደገደገች እየተረመረመች
ትግል ያማጠችበት
አዎ! ተደራጅቶ መታገልን
ተደራጅቶ መታጠቅን
ታጥቆ መቆራቆስን
ሰይፍ ጥሎ መሞትን
በሞት ሕይወትን ማግኘትን
አርነትን ነፃነትን ድልን መቀዳጀትን
አውቄሃለሁ፣ እወቁበት
አጢኛለሁ፣ አጢኑበት
ተምሬሃለሁ፣ ተማሩበት
እያልን
ለአርሶ አደሩ ቤዛ ሊሆን፣
መሪው ሊሆን፣ ተክሉ ሊሆን
ለጭቁኖች ተገን ሊሆን
ጋሻ ሊሆን፣
ደጀን ሊሆን
ወግ አደጉ ጀግና
ሲድህ ከርሞ ተበራቶ
አገር አቀፍ ተልዕኮውን
ፕሮግራሙን ረጭቶ
እራሱን ይፋ ያወጣበት
እራሱን አዋጅ ያወጀበት
ፋሽስቶችን እንደ ድንገት
ባንዳዎችን እንደ ቅጽበት
ሳያስቡት፣ ሳያልሙት
ኩም! ስቅቅ! ያረገበት
በሠራ አከላታቸው ሽብር የለቀቀበት
ለምዝብሮች፣ ለጭቁኖች
በአለኝታነት የቆመበት
ያዲስ ሥርዓት አዲስ ተስፋን
በውን፣ በወግ ያሳየበት
እነሆ! ዛሬ አርባ ዓመት
. . . እነሆ ዛሬ አርባ ዓመት።

ዋቢ ማጣቀሻ፣

- ነሲቡ ስብሐት፣ "ፍፁም ነው እምነቴ" **ቀይ ሽብር** የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ፤ መስከረም 2007 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ።
- የኢሕአፓ ሦስተኛ ዓመት መታሰቢያ ግጥም፣ ነሕሴ 26 ቀን 1970 ዓ.ም.።

«ያ ትውልድ ተቋም»

ነሐሴ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ.ም.

(September 1, 2015)